# የደጀን ከተማ ነዋሪዎች ድብደባ እንደ ተፈፀመባቸው ተሰማ

በምሥራቅ ጎጃም ዞን በደጀን ወረዳ የደጀን ከተማ ነዋሪዎች እንዲሁም በሥራ ምክንያት በከተማው ውስጥ የተገኙ ባለጉዳዮች ሁሉ በፖሊሶችና በአካባቢው ታጣቂዎች ነሐሴ 15 ቀን 2000 ዓ.ም ከፍተኛ ድብደባ እንደተፈፀመባቸው ተሰማ።

በዕለቱ ታጣቂዎቹ የተመደበላቸውን ቦታ በስምሪት ይዘው ከቆዮ በኋላ ከምሽቱ 2 ሰዓት ተኩል ሲሆን የከተማውን መብራት በማጥፋት በከተማ ውስጥ ለግል ጉዳይ በመንቀሳቀስ ላይ የነበረውን ሰላማዊ ሰው ሁሉ በዱላ መቀጥቀጥ እንደ ጀመሩ የዓይን ምሥክሮች አረጋግጠዋል።

በዚህ ወቅት በዋናነት ድበደባውን የፈፀሙት 1. ወታደር ሙሉቀን ደያስ 2. ወታደር ዓለም 3. ወታደር ከበደ 4. ታጣቂ እንዳለው ተረፈ 5. ታጣቂ ድረስ በፈቃዱና ሌሎች ሶስት ታጣቂዎች እንደነበሩ ታውቋል።

እንደ መረጃ ምንጮች አገላለፅ የጅምላ ድብደባው የተጀመረው በደጀን ከተማ ውስጥ የሚገኙ ድንጋይ ጫኛች፤ ተሸካሚዎች፤ የቀን ሠራተኛች፤ ጫማ ጠራጊዎችና ጎዳና ተዳዳሪዎች የብሔረ አማራ ደሞክራሲያዊ ንቅናቄ /የብአደን/ አባል እንዲሆኑ ተጠይቀው ፈቃደኛ ሳይሆኑ በመቅረታቸው እንደሆነ ታውቋል።

ቀደም ሲል በእነዚህ የሙያ መስኮች የተሰማሩ የከተማ ነዋሪዎችን ብድር እንደሚሰጣቸው ተናግረው የአገዛዙ አካላት አደራጅተዋቸው እንደነበርም ምንጮች አስታውቀዋል።

በዕለቱ በተፈፀመው ከፍተኛ ድብደባ ጉዳት ከደረሰባቸው መካከል 1. ጌትሽ ክብረት 2. መሐመድ ጌትነት 3. አልዩ ይማምና 4. አዲሱ ታመነ የተባሉ ወጣቶች ይገኙባቸዋል።



Ethiolion.com